በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን
Federal Democratic Republic of Ethiopia
CIVIL SERVICE COMMISSION

ቁጥር/Ref.No. ሲሠሆ/ሃሲ/113/2012

ቀን/ Date 17 ታህሳስ 2012

ለክልሎችና ለሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች
ትምህርት ቢሮዎች
ባሉበት

የመምህራን፣ የርዕሳነ መምህራን እና ሱፐርቫይዘር የሥራ ዝርዝር መግለጫዎች በነጥብ የሥራ ምዘና ዘዴ ተመዝነው ውጤቱን ሐምሌ 11 ቀን 2011 ዓ.ም. በቁጥር 499/2013 እና ታህሣስ 1 ቀን 2012 ዓ.ም. በቁጥር ሲሰኮ/ኮቢ/80/2012 በተፃፉ ደብዳቤዎች ሸኚነት ለትምህርት ሚኒስቴር ተልኳል።

በምዘና ውጤቱ ላይ ከሚኒስቴሩ የበላይ አመራሮች፣ የሥራ ኃላፊዎች፣ ባለሙያዎችና ከመምህራን ማህበር ተወካዮች ጋር በተለያዩ መድረኮች በዝርዝር በመወያየት፣ የተገኙ ግብዓቶችን በመጠቀምና የሥራ ዝርዝር መግለጫዎችን ዳግም አዳብሮ እንዲመዘኑ ከተደረገ በኋላ ስምምነት ላይ የተደረሰበት ውጤት ተግባራዊ እንዲደረግ ከዚህ ዝርዝር የድልድል አፈፃፀም መመሪያ ጋር አያይዘን መላካችንን እንገልፃለን።

ከሠላምታ ጋር

በዛብህ ገብረየስ በየነ
ኮሚሽነር

ግልባጭ
- ለጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት
- በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት
  ለሰው ሀብት ልማትና ቴክኖሎጂ
  ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ
- ለትምህርት ሚኒስቴር
  አዲስ አበባ
- ለክልሎችና ለሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች
  ሲቪል ሰርቪስ ቢሮዎች
  ባሉበት

# የመምህራን፣ የርዕሳነ መምህራንና ሱፐርቫይዘር የሥራ መደቦች የድልድል አፈጻጸም መመሪያ

ቁጥር 499/2013

ታህሳስ 2012 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

## መግቢያ፡

ለረጅም ዓመታት ይሠራበት የነበረውን የሥራ ምደባ ዘዴን በማስቀረት አዲስ የነጥብ የሥራ ምዘና ዘዴን በመጠቀም በሀገራችን ያሉ የሥራ መደቦች በተመሳሳይ መመዘኛዎች (Factors) ተመዝነው ደረጃ እና ደመወዝ እንዲወስን ለማድረግ በየሴክተር መ/ቤቶች ላሉ የሥራ መደቦች የሥራ ዝርዝር የማዘጋጀት ሥራ በሲቪል ስርቪስ ኮሚሽን አስተባባሪነት ሲከናወን ቆይቶ ተጠናቅቋል፡፡

የዘርፉን ባለሙያዎች፣ መምህራንን፣ ርዕሳነ መምህራንን፣ ሱፐርቫይዘሮችን እና የመምህራን ማህበር አባላትን በማሳተፍ ለቅድመ መደበኛ፣ ለአንደኛ እና ለሁለተኛ ደረጃ መምህራን፣ ርዕሳነ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች የሥራ ዝርዝር መግለጫዎች በነጥብ የሥራ ምዘና ዘዴ በማዘጋጀት እንዲመዘኑ ተደርጓል፡፡ የትምህርት ሙያተኞቹን ከነባር የዕድገት መሰላሎች አዲስ ወደተዘጋጁት በማሸጋገር ድልድል ለማድረግ እንዲረዳ ደረጃ ለወጣላቸው መምህራን፣ ርዕሳነ መምህራን እና ሱፐርቫይዘሮች ይህ የአፈፃፀም መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Civil Service Commission

በዛብህ ገብረየስ በየነ
ኮሚሽነር

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ የድልድል አፈፃፀም መመሪያ በነጥብ የሥራ ምዘና ዘዴ ተመዝነው ደረጃ በወጣላቸው "የመምህራን፣ የርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘር የሥራ መደቦች የድልድል አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 499/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፣

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ የድልድል መመሪያ፡-

"የትምህርት ሙያ" ማለት በትምህርት ሚኒስቴር እውቅና የተሰጠው ሥልጠና ፕሮግራም ሆኖ ለመምህራን ስልጠና በተዘጋጀው የሥርዓተ ትምህርት ሥልጠና ማዕቀፍ በማለፍ በነጥብ የሥራ ምዘና ዘዴ በትምህርት ሚኒስቴር የሥራ ዝርዝር የተዘጋጀለት፣ በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ተመዝኖ ደረጃ የወጣለት እና በዓቢይ የሙያ ዘርፍ 06 የተካተተ ሙያ ነው፡፡

"ዓቢይ የሙያ ዘርፍ" ማለት በነጥብ የሥራ ምዘና ዘዴ ተመዝነው ደረጃ የወጣላቸው የሥራ መደቦች እንደየባህርያቸውና የሙያ ተመሳሳይነታቸው እየተለዩ በአንድነት የተሰባሰቡበት ዋና የሥራ መደቦች ቤተሰብ መለያ ነው፡፡

"የነጥብ የሥራ ምዘና ዘዴ" ማለት የሥራ መደቦችን ለመመዘን በተዘጋጁ መስፈርቶች ሥራዎችን መዝኖ ደረጃና ዋጋቸውን መተመኛ ስልት ነው፡፡

### 3. የጾታ አገላለጽ

በዚህ መመሪያ ውስጥ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴት ጾታንም ያካትታል፣

### 4. የመመሪያው ተፈጻሚነት

ይህ የድልድል አፈጻጸም መመሪያ ተፈጻሚ የሚሆነው በትምህርት ሙያ መደቦች ላይ ብቻ ነው፡፡

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Civil Service Commission

በዛብህ ገብረየስ በየነ
ኮሚሽነር

## ክፍል ሁለት

### 5. ዝርዝርመመሪያ

1. የመምህራን ድልድል የሚደረገው በነጥብ የሥራ ምዘና ዘዴ ተመዝነው ደረጃ በወጣላቸው የሥራ መደቦች ላይ ብቻ ነው፡፡

2. በሁሉም የትምህርት እርከኖች የመምህራን፣ የርዕሳነ መምህራን እና ሱፐርቫይዘር የሥራ ተዋረዶች፡

**ሀ) መምህር**

- ጀማሪ መምህር
- መለስተኛ መምህር
- መምህር
- ከፍተኛ መምህር
- ተባባሪ መምህር
- መሪ መምህር
- ከፍተኛ መሪ መምህር

**ለ) ርዕሰ መምህር**

- ምክ/ ርዕሰ መምህር
- ርዕሰ መምህር

**ሐ) ሱፐርቫይዘር**

- ሱፐርቫይዘር
- ከፍተኛ ሱፐርቫይዘር

ናቸው፡፡

በዛብህ ገብረየስ በየነ
ኮሚሽነር

3. ሠርተፊኬት ወይም ደረጃ I ወይም ደረጃII የትምህርት ደረጃ ኖሯቸው የዲፕሎማ ወይም የመጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት ደረጃ በሚጠይቅ የትምህርት እርከን ላይ የሚያገለግሉ መምህራን የደረጃ እድገታቸው የትምህርት ደረጃቸው በሚፈቅድላቸው የትምህርት እርከን መሠረት መጠሪያ፣ ደረጃና ደመወዛቸው ይወሰናል፡፡

4. ዲፕሎማ ወይም ደረጃ III ወይም ደረጃ IV የትምህርት ደረጃ ኖሯቸው የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም የ2ኛ ዲግሪ የትምህርት ደረጃ በሚጠይቅ የትምህርት እርከን ላይ የሚያገለግሉ መምህራን የደረጃ እድገታቸው የትምህርት ደረጃቸው በሚፈቅድላቸው የትምህርት እርከን መሠረት መጠሪያ፣ ደረጃና ደመወዛቸው ይወሰናል፡፡

5. የመጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት ደረጃ ኖሯቸው የ2ኛ ዲግሪ በሚጠይቅ የትምህርት እርከን ላይ የሚያገለግሉ መምህራን የደረጃ እድገታቸው የትምህርት ደረጃቸው በሚፈቅድላቸው የትምህርት እርከን መሠረት መጠሪያ፣ ደረጃና ደመወዛቸው ይወሰናል፡፡

6. ከተመደቡበት የትምህርት እርከን በላይ የትምህርት ደረጃኖሯቸው ዝቅ ባለ የትምህርት እርከን በማገልገል ላይ ያሉ መምህራንን በተመለከተ፡-

   ሀ) ለመምህራን ሥልጠና በተዘጋጀው የሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ ወጪው በመንግሥት ተሸፍኖ ወይም በመንግሥት ዋስትና የሰለጠኑ መምህራን ለትምህርት ደረጃቸው ወደ ሚመጥን የትምህርት እርከን ተዛውረው እንዲሠሩ ወይም የትምህርት ደረጃቸው በሚመጥን እርከን መሠረት መጠሪያ፣ ደረጃ እና ደመወዛቸው ይወሰናል፡፡

   ለ) በግላቸው ለመምህራን ሥልጠና በተዘጋጀው የሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ በመንግሥት የትምህርት ተቋም ሠልጥነው የትምህርት ደረጃቸውን ያሻሻሉና ከተመደቡበት የትምህርት እርከን በላይ የትምህርት ደረጃ ኖሮአቸው ዝቅ ባለ የትምህርት እርከን በማገልገል ላይ ያሉ መምህራን የተማሩት የትምህርት ዓይነት ከሚያስተምሩት የትምህርት ዓይነት ጋር ተመሳሳይና ተፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ሥራና ሠራተኛን ለማገናኘት ሲባል ክፍት የሥራ መደብ ላይ ተዛውረው የትምህርት ደረጃቸው በሚፈቅድላቸው የትምህርት እርከን መሠረት መጠሪያ፣ ደረጃ እና ደመወዛቸው ይወሰናል፡፡

በዛብህ ገብረየስ በየነ
ኮሚሽነር

ሐ) በግላቸው ለመምህራን ሥልጠና በተዘጋጀው የሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ በመንግሥት የትምህርት ተቋም ሰልጥነው የትምህርት ደረጃቸውን ያሻሻሉና ከተመደቡበት የትምህርት እርከን በላይ የትምህርት ደረጃ ኖሯቸው ዝቅ ባለ የትምህርት እርከን በማገልገል ላይ ያሉ መምህራን የትምህርት ዓይነታቸው ተፈላጊ ሆኖ በሙያቸው ከፍ ወዳለ የትምህርት እርከን ተዛውረው እንዲሠሩ ሲመደቡ ወደ ተመደቡበት ቦታና እርከን ተዛውረው ለማገልገል ፈቃደኛ ካልሆኑ ያሉበት ደረጃ በሚጠይቀው የትምህርት ደረጃ፣ መጠሪያና ደመወዛቸው ይወሰናል፡፡

7. ከላይ በተራ ቁጥር 4 በተጠቀሰው ሁኔታ የተደለደሉና ከሀምሌ 2011 ዓ.ም. በፊት የደረጃ እድገት ያገኙ መምህራን፤ ርዕሳነ መምህራን እና ሱፐርቫይዘሮች የመጨረሻውን የደረጃ እድገት ካገኙበት ጊዜ ጀምሮ ያበረከቱት አገልግሎት ለቀጣይ የደረጃ እድገት ይያዝላቸዋል፡፡

8. በነባር የመምህራን የደረጃ ዕድገት መመሪያ መሠረት ይሰጥ የነበረው የደረጃ እድገት የሚቀጥል ይሆናል፡፡

9. በነጥብ የሥራ ምዘና ዘዴ ተመዝነው ደረጃ በወጣላቸው የመምህራን፣ የርዕሳነ መምህራን እና ሱፐርቫይዘር የሥራ መደቦች ላይ ድልድል የሚፈጸመው ያለውድድር ሲሆን፣ ለመደልደል አሁን የደረሰበትን ደረጃ ወይም የካርየር እድገት ያገኘበትን ጊዜ የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

10. ሀምሌ 1 ቀን 2011 ዓ.ም. የደረጃ እድገት ማግኘት ያለባቸው መምህራን፣ ምክ/ ርዕሰ መምህራን፣ ርዕሰ መምህራን እና ሱፐርቫይዘሮች በቅድሚያ የደረጃ ዕድገት ከተሰጣቸው በኋላ በነጥብ የሥራ ምዘና ዘዴ ወደ ተመዘኑ የሥራ ደረጃዎች እንዲሸጋገሩ በማድረግ በነጥብ የሥራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ጥናት የደመወዝ ስኬል አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 1/2012 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የደመወዝ ስኬል መሸጋገሪያ ይከፈላቸዋል፡፡

በዛብህ ገብረየስ በየነ
ኮሚሽነር

11.ከነባር የመምህራን የዕድገት መሰላል መካከል የመጨረሻ ሁለት ተዋረዶች (ከፍተኛ መሪ መምህር II እና ከፍተኛ መሪ መምህር III) ስለታጠፉ፣ ይህ መመሪያ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት ከፍተኛ መሪ መምህር I ወይም ከፍተኛ መሪ መምህር II የዕድገት መሰላል ላይ ደርሰው ከጥር 2012 ዓ.ም. እስከ ጥር 2014 ዓ.ም. ተፈላጊውን የመቆያ ጊዜ እና ሌሎች መስፈርቶችን አሟልተው በነባሩ የዕድገት መሰላል ከፍተኛ መሪ መምህር II እና ከፍተኛ መሪ መምህር IIIደረጃ ላይ መድረስ የነበረባቸው መምህራን ከፍተኛ መሪ መምህር ሆነው ሲመደቡ፣ ከሥራ መደቡ የመነሻ ደመወዝ ወይም የመነሻ ደመወዙን ደርሰውበት ወይም አልፈውት ከሆነ በሚከፈላቸው የወር ደመወዝ ላይ 3 ተጨማሪ እርከን ይሰጣቸዋል፡፡

12.በዚህ የድልድል አፈጻጸም መመሪያ የመምህራን የሥራ መደቦች ከነባሩ የዕድገት መሰላል አዲስ ወደተዘጋጁ የሥራ መደቦች ሲሸጋገሩ እንደየሥራ መደቦቹ የእድገት መሰላል ርዝመት የተወሰኑት ነባር ደረጃዎች በመጣመር ከዚህ በታች በሚገኘው ሠንጠረዥ-1 መሠረት ድልድላቸው በአዲሶቹ የሙያ ተዋረዶች ላይ ይፈጸማል፡፡

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Civil Service Commission

በዛብህ ገብረየስ በየነ
ኮሚሽነር

## ሠንጠረዥ 1

## የመምህራን መሸጋገሪያ ሠንጠረዥ

| ተራ ቁ | ነባር የሥራ መደብ | አዲስ የሥራ መደብ |
|---|---|---|
| 1 | ጀማሪ መምህር | ጀማሪ መምህር |
| 2 | መለስተኛ መምህር | መለስተኛ መምህር |
| 3 | መምህር | መምህር |
| 4 | ከፍተኛ መምህር | ከፍተኛ መምህር |
| 5 | ተባባሪ መሪ መምህር | ተባባሪ መሪ መምህር |
| 6 | መሪ መምህር | መሪ መምህር |
| 7 | ከፍተኛ መሪ መምህር I | ከፍተኛ መሪ መምህር |
| 8 | ከፍተኛ መሪ መምህር II | |
| 9 | ከፍተኛ መሪ መምህር III | |

13. ለአንደኛ ደረጃና ለ2ኛ ደረጃ ምክ/ ርዕሰ መምህር የሥራ መደቦች ልዩ ድጋፍ በሚሹ ክልሎችና በልማት ወደ ኋላ በመቅረት ወይም ከጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ ምቹ አለመሆን ጋር ተያይዞ ለኑሮ አስቸጋሪ በሆኑ የሥራ ቦታዎች ከፍተኛ መምህር ደረጃ ላይ ከደረሱ መምህራን ጀምሮ፣ በሌሎች ክልሎችና የከተማ አስተዳድሮች ደግሞ መሪ መምህር ደረጃ ላይ ከደረሱ መምህራን ጀምሮ ተወዳድረው ይመደባሉ፡፡

14. በነባሩ የደረጃ እድገት መሰላል ስያሜ መሠረት (ሐምሌ 01 ቀን 2008 ዓ.ም በወጣው መሠረት) በመጀመሪያ እና በ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በምክ./ ርዕሰ መምህርነትና በርዕሰ መምህርነት በተለያዩ የእድገት መሰላሎች ደረጃ እያገለገሉ ላሉት ከነባሩ የሥራ ደረጃ በነጥብ የሥራ ምዘና ዘዴ ወደ ተመዘኑ የሥራ መደቦች የሚደረገው ሽግግር ከዚህ ቀጥሎ እንደተመለከተው የሚፈጸም ይሆናል፡፡

በዛብህ ገብረየስ በየነ
ኮሚሽነር

ሀ) ነባር የምክ/ ርዕሰ መምህራንና ርዕሰ መምህራን የዕድገት መሰላሎች ስለታጠፉ በነባሩ አመዳደብ ጀማሪ ምክ./ ርዕሰመምህር፣ ምክ/ ርዕሰ መምህር፣ ከፍተኛ ምክ/ ርዕሰ መምህር ደረጃ ላይ ያሉ፣ እንደዚሁም ጀማሪ ርዕሰ መምህር፣ ርዕሰ መምህር እና ከፍተኛ ርዕሰ መምህር ደረጃ ላይ ያሉ በአዲሱ የነጥብ የሥራ ምዘና ደረጃ አወሳሰን በቅደም-ተከተል ምክ/ ርዕሰ መምህር እና ርዕሰ መምህር የሥራ ደረጃ ላይ ይደለደላሉ፡፡

ለ) በነባሩ የምክ./ ርዕሰ መምህራንና ርዕሰ መምህራን የዕድገት መሰላሎች ከመሪ ምክ./ ርዕሰ መምህር I፣ II፣ III እና መሪ ርዕሰ መምህር I፣ II፣ III ላይ መድረስ የነበረባቸው በነጥብ የሥራ ምዘና ደረጃ አወሳሰን በቅደም ተከተል ምክ/ ርዕሰ መምህር ወይም ርዕሰ መምህር ሆነው የሚመደቡ ሆኖ የሥራ መደቡ የመነሻ ደመወዝ ወይም የመነሻ ደመወዙን ደርሰውበት ወይም አልፈውት ከሆነ በሚከፈላቸው የወር ደመወዝ ላይ 3 /ሶስት/ ተጨማሪ እርከን ይሰጣቸዋል፡፡

ሐ) ከጥር 2012 ዓ.ም. እስከ ጥር 2014 ዓ.ም. ተፈላጊውን የመቆያ ጊዜ እና ሌሎች መስፈርቶችን አሟልተው በነባሩ የዕድገት መሰላል መሪ ምክ/ ርዕሰ መምህር I፣ መሪ ምክ./ ርዕሰ መምህር II እና መሪ ምክ/ ርዕሰ መምህር III እንዲሁም መሪ ርዕሰ መምህር I፣ መሪ ርዕሰ መምህር II እና መሪ ርዕሰ መምህር III ደረጃ ላይ መድረስ ያለባቸው ምክ/ ርዕሰ መምህራንና ርዕሰ መምህራን በአዲሱ የነጥብ የሥራ ምዘና አወሳሰን መሠረት ምክ/ርዕሰ መምህር እና ርዕሰ መምህር (በቅደም ተከተል) ሆነው ሲመደቡ የሥራ መደቡ የመነሻ ደመወዝ የሚሰጣቸው ይሆናል፡፡

15. በነባሩ የደረጃ እድገት መሰላል ስያሜ (ሐምሌ 01 ቀን 2008 ዓ.ም. በወጣው) መሠረት በ1ኛ እና በ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በተለያዩ ደረጃዎች ማለትም በተባባሪ ሱፐርቫይዘርነት፣ በሱፐርቫይዘርነት፣ በከፍተኛ ሱፐርቫይዘር I፣ በከፍተኛ ሱፐርቫይዘር II እና በከፍተኛ ሱፐርቫይዘር III እያገለገሉ ያሉ ከዚህ ቀጥሎ እንደተመለከተው የሚፈጸም ይሆናል፡፡

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Civil Service Commission

በዛብህ ገብረየስ በየነ
ኮሚሽነር

ሀ) ተባባሪ ሱፐርቫይዘር እና ሱፐርቫይዘር ደረጃ ላይ ያሉ በአዲሱ የሥራ ምዘና ደረጃ አወሳሰን ሱፐርቫይዘር በሚለው የሥራ ደረጃ ላይ ይደለደላሉ፡፡

ለ) ከፍተኛ ሱፐርቫይዘር I፣ II እና III ደረጃ ላይ የደረሱ በአዲሱ የሥራ ምዘና ደረጃ አወሳሰን ከፍተኛ ሱፐርቫይዘር ሆነው ይደለደላሉ፡፡

16. በዚህ የድልድል አፈጻጸም መመሪያ የምክ/ ርዕሰ መምህራን፣ የርዕሰ መምህራን እና ሱፐርቫይዘር የሥራ መደቦች ከነባሩ የዕድገት መሰላል አዲስ ወደ ተዘጋጁ የሥራ መደቦች ሲሸጋገሩ እንደየሥራ መደቦቹ የእድገት መሰላል ርዝመት የተወሰኑት ነባር ደረጃዎች በመጣመር ከዚህ በታች በሚገኘው ሠንጠረዥ-2 መሠረት ድልድላቸው በአዲሶቹ የሙያ ተዋረዶች ላይ ይፈጸማል፡፡

### ሠንጠረዥ 2
### የምክ/ ርዕሰ መምህር፣ ርዕሰ መምህር እና ሱፐርቫይዘሮች መሸጋገሪያ ሠንጠረዥ

| ተራ ቁ | ነባር የሥራ መደብ | አዲስ የሥራ መደብ |
|---|---|---|
| 1 | ጀማሪ ምክ./ ርዕሰ መምህር | ምክትል ርዕሰ መምህር |
| 2 | ምክ/ ርዕሰ መምህር | |
| 3 | ከፍተኛ ምክ/ ርዕሰ መምህር | |
| 4 | መሪ ምክ/ ርዕሰ መምህር I | |
| 5 | መሪ ምክ/ ርዕሰ መምህር II | |
| 6 | መሪ ምክ/ ርዕሰ መምህር III | |
| 7 | ጀማሪ ርዕሰ መምህር | ርዕሰ መምህር |
| 8 | ርዕሰ መምህር | |
| 9 | ከፍተኛ ርዕሰ መምህር | |
| 10 | መሪ ርዕሰ መምህር I | |
| 11 | መሪ ርዕሰ መምህር II | |
| 12 | መሪ ርዕሰ መምህር III | |
| 13 | ተባባሪ ሱፐርቫይዘር | ሱፐርቫይዘር |
| 14 | ሱፐርቫይዘር | |
| 15 | ከፍተኛ ሱፐርቫይዘር I | ከፍተኛ ሱፐርቫይዘር |
| 16 | ከፍተኛ ሱፐርቫይዘር II | |
| 17 | ከፍተኛ ሱፐርቫይዘር III | |

በዛብህ ገብረየስ በየነ
ኮሚሽነር

17. **ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች**

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ በዚህ መመሪያ ውስጥ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

18. **ተጠያቂነት**

የዚህ መመሪያን ድንጋጌዎች በመተላለፍ ተመዝኖ ደረጃ ባልወጣለት የሥራ መደብ ላይ የሠራተኛ ድልድል የሚፈጽም ኃላፊ አግባብ ባለው ህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

19. **በዚህ መመሪያ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች**

በዚህ መመሪያ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ጥያቄው ለኮሚሽኑ እየቀረበ ውሳኔ የሚሰጥበት ይሆናል።

20. **የመመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከሐምሌ 1 ቀን 2011 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**በዛብህ ገብረየስ**
**የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን**
**ኮሚሽነር**

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Civil Service Commission

በዛብህ ገብረየስ በየነ
ኮሚሽነር

## ሠንጠረዥ - 3

### በየደረጃው ያሉ መምህራን፣ ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች የምዘና ውጤት

| ደረጃ | መምህር | | | | ርዕሰ መምህር | | ሱፐርቫይዘር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ሠርተፊኬት | ዲፕሎማ | ዲግሪ (ከ1-8ኛ) | ማስተርስ (ከ9-12ኛ) | የመጀመሪያ ደረጃ | 2ኛ ደረጃ | የመጀመሪያ ደረጃ | 2ኛ ደረጃ |
| VIII | ጀማሪመምህር | | | | | | | |
| IX | መለስተኛ መምህር | ጀማሪ መምህር | | | | | | |
| X | መምህር | መለስተኛ መምህር | ጀማሪ መምህር | | | | | |
| XI | ከፍተኛ መምህር | መምህር | መለስተኛ መምህር | ጀማሪ መምህር | | | | |
| XII | ተባ/ መሪ መምህር | ከፍተኛ መምህር | መምህር | መለስተኛ መምህር | | | | |
| XIII | መሪ መምህር | ተባ/ መሪ መምህር | ከፍተኛ መምህር | መምህር | | | | |
| XIV | ከፍ/ መሪ መምህር | መሪ መምህር | ተባ/ መሪ መምህር | ከፍተኛ መምህር | | | | |
| XV | | ከፍ/ መሪ መምህር | መሪ መምህር | ተባ/ መሪ መምህር | | | | |
| XVI | | | ከፍተኛ መሪ መምህር | መሪ መምህር | ምክ./ርዕሰ መምህር | | ሱፐርቫይዘር | |
| XVII | | | | ከፍ/ መሪ መምህር | ርዕሰ መምህር | ምክ./ ርዕሰ መምህር | ከፍ/ ሱፐርቫይዘር | ሱፐርቫይዘር |
| XVIII | | | | | | ርዕሰ መምህር | | ከፍተኛ ሱፐርቫይዘር |

በዛብህ ገብረየስ በየነ
ኮሚሽነር